# ኢትዮጵያችን

*የአንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 4 ቁጥር 3 ኅዳር ፲፪ ቀን ፪ ሺህ ፲፪ ዓ.ም.

## “የነበረ፣ ያለና ወደፊትም የሚኖር?”

*የድምጽ ቅጂውን ለማድመጥ እዚህ ይጫኑ ( https://www.youtube.com/watch?v=dljFG3l7s9g&t=0s )*

***“አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ”*** ለሀገርና ሕዝብ ድምጻችንን እስካሰማን ድረስ መንግሥት በሚወረውረው አጀንዳ ሕዝብ እንዳይዘናጋ፣ የሚሉትና የሚጓዙበት አቅጣጫ ግራ ለገባቸው ፖለቲከኞች፣ ለሚዘላብዱ አንዳንድ ምሁራን፣ የተናገሩት ሁሉ መሬት ጠብ የማይል ለሚመስላቸው የመንግሥት ባለሥልጣናትና መሪዎች እይታችንን እናስነብባለን፣ መደረግ ያለበትን እንጠቁማለን:: ፖለቲከኞች ነንና እንቀሰቅሳለን፣ እንታገላለን፣ እናታግላለን። የምንታገለው ለሕዝቧ ለሆነች ኢትዮጵያ ነውና ትግላችንም የዘር ዕልቂትና ሽብር ከሚያካሂዱ ኃይሎችና ለዚህም ከለላና ተገን ከሆናቸው የ28 ዓመቱ የኢሕአዴግ ዘረኛ አገዛዝና ሕገ መንግሥት መወገድ ነው።

ሰሞኑን ጠ/ሚር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የሰጡትን ጋዜጣዊ መግለጫና የአመራር ዕቅዳቸውን ለማሳካት የሚጓዙባቸውን አቅጣጫዎችና በየመድረኩ የሚሠነዝሯቸውን ሀሳቦችና አባባሎች ተገን ያደረገ መልዕክታችን እነሆ!

### *<u>ዘረኝነት በዩንቨርስቲዎች</u>*

በኢትዮጵያችን እየተካሄደ ያለው የዘር ማጥፋትና አሸባሪነት ተግባር ውይይት ቢሉት፣ በጋራ ተስማማን በሉት፣ ውህደት ቢባል 28 ዓመት ሥር የሰደደ የዘረኝነት አገዛዝ እስካልተወገደ ድረስ “ከክልላችን ውጡ፣ ክልላችንን ስጡን፣ እኛም ክልል እንሁን፣ የመገንጠል መብታችን ይጠበቅ፣” መሰል ጥያቄዎች አይቋረጤ ናቸው። ዛሬ የዘር ፍትጊያ በየክልሉ ያሉ ዩንቨርስቲዎችን እያመሰ ይገኛል። ወጣት ተማሪዎች እየተደበደቡበት፣ ሴቶች እየተደፈሩበት፣ አዛውንት እየታረዱ፣ እየተገደሉ፣ ከሮቅ ተወረወረ፣ ተከበናል፣ በፍርሃት ውስጥ ነን ድረሱልን፣ ድምጻችንን አሰሙልን የሚነፍስባቸው ዩንቨርስቲዎች እራሳቸው ወደ ክልልነት እየተቀየሩ ይመስላል። ዘረኝነት ዕድሜ ከሰጠው ለአማራ፣ ለትግሬ፣ ለኦሮሞ ለሌላውም የሌላውን ዘር የማያካትት የዘር ዩንቨርስቲ ብቻ ተግባራዊ እንደሚሆን መገመት አዋቂ አያሰኝም። ከተሳካላቸው ወደድንም ጠላን የዘረኝነት የመጨረሻው ደረጃ ሀገር መበታተን ነው። ዛሬ የምናየው ይህንኑ ነው። ዘረኝነቱ ከእምነት ጋር ሲጣመር ማየት ደግሞ ሌላው አስከፊ ገጽታ መሆኑ በተግባር እየታየ ነው። በየዩንቨርስቲው የተከሰተውን ዘርን ተገን ያደረገ ጥቃት ለመግታት “ዩንቨርስቲዎችን መዝጋት” መፍትሄ አይደለም። ይልቁንስ ወደ ሌሎች ዩንቨርስቲዎች እንዲሁም ወደ ሌሎች ኮሌጆች፣ ከፍተኛና መለስተኛ ትምህርት ቤቶች በተጨማሪም ወደ ሕጻናት መዋያ ጭምር እንደ ወረርሽኝ እንዳይዛመት ለሚታወቀው ችግር መድሐኒቱን መስጠት ከመንግሥት ይጠበቃል። የቅድሚያ አስቸኳይ እርምጃ በአደባባይ ሀገርና ሕዝብ አጥፊ ቅስቀሳውን እያደረገ “ጨርሷቸው! በሜንጫ በሏቸው!” ባዩን አሸባሪ ጀዋር አሕመድን

*ወደ ሕግ ማቅረብ። እንደ መንግሥት መወሰድ የሚገባው እርምጃ እየታወቀ የትምህርት ተቋማትን በመዝጋት የ10 ዓመቱ የልማት እቅድ እንዳይራዘም ያለንን ስጋት እንጠቁማለን።*

*ዘረኝነት በዚህ ጉዞው ከትምህርት ቤቶች እድገት አሳይቶ ወደ መሥሪያቤቶች የተዛመት ዕለት ግራ የተጋባው መንግሥት እራሱ የሥራ ማቆም አድማ እንዳያውጅና ፈገግ እንዳያስደርገን እንሰጋለን። የዘረኝነት በሽታ ግንድ የሆነውን ሕገ መንግሥት ማሻሻል ሳይሆን ድባቅ! መምታት ካልተቻለ ሀገር እየታመሰች፣ ሕዝብ እየተሰቃየ ከመቀጠል አልፎ መበታተን ወይም መኖራቸው እተዘነጋው የአፍሪካ ሀገሮች ውስጥ እንዳንመደብ አስቀድመን ልናስገነዝብ እንወዳለን። ወያኔ ሰራሹን የኢሕአዴግ ሕገ መንግሥት የመቀየር ምክራችንን ግና "ሰማይ ይወድቃል" ብሎ ምሰሶ ይዞ እንደቆመው ሞኝ ያስቆጥረናል። ለካ! ኢሕአዴግ እና ሕገ መንግሥቱ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጾች መሆናቸውን ዘንግተነዋልሳ።*

***<u>የዘር ፖለቲካ ድርጅቶች ዘረኝነት ላይ ሊዘምቱ?</u>***

*ሌላው የሰሞኑ ዜና የዘር ፖለቲከኞች ዘረኝነት ላይ ሊዘምቱ መግባባታቸው ነው። "እሾህን በሾህ" የሚባለው የሀገራችን ሊቆች ያወረሱን ተረት ዓይነት ማለት ነው። "እሾህን በወረንጦ" ቢሆን ግን ዘረኝነት ሙሉ በሙሉ ቦታውን ለኢትዮጵያዊነት እያስረከበ በሄደ ነበር። እኛ የዘር ዕልቂት በሀገራችን ስንቃኝ የሰሞኑን ብቻ አንመለከተውም። መነሻችን የዛሬ 28 ዓመቱ የበደኖና አርባ ጉጉ ዕልቂት ነው። በቀጣይነት በጅማ፣ በኢሉባቦር፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ወገኖቻችን በተለያየ ጊዜያት የደረሰውን ዕልቂት፣ በአሸባሪ ስም የምሥራቁ የሀገራችን ክፍል ወገኖቻችን ላይ የዘነበው ጥይትና ቦምብ ሳንረሳው ነው። የበደኖና አርባ ጉጉን እልቂት ገና ከጅምሩ በጫጉላ ፍቅራቸው ወቅት በህወሓት ከለላነት የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ተግብሮት በእርድ የፈሰሰው የንጹሀን ደም፣ ከገደል አፋፍ ተወርውረው እዛው የቀሩ ኢትዮጵያውያንን ሳንዘነጋ ነው። ዛሬም እንደትላንቱ የመንግሥት ጥበቃና ከለላ የተሰጠው አሸባሪው ጀዋር በአንድ በኩል፣ በኦሮሚያ ስም ኢትዮጵያን ሊያፈራርስ የተዘጋጀው ኦነግ በሌላ በኩል ከሌሎች ተባብረው እራሳቸው የሚያደርጉትን ዕልቂት በውይይት ሊያስቆሙ ጠረጴዛ ሲከቡ "ጥሩ ጅምር" ለማለት "እስቲ እንያቸው" ለሚሉት መከራከሪያ አጀንዳ ይሆን ይሆናል እንጂ ከቶም የዘርና ቋንቋን አከላለል ፈቀቅ አያደርገውም።*

***<u>የሀገራችን ዋናና መሠረታዊ ችግር ሀገርን በዘርና ቋንቋ ሸንሽኖ፣ አንዱ ጎሳ/ነገድ ከሌላው እንዳይግባባ ገድቦ፣ አማራን በጠላትነት ፈርጆ፣ አብያተ ቤተ ክርስቲያናት ላይ አነጣጥሮ፣ ዓለም የመሰከረላቸውን የምንሊክ ፀረ ቅኝ አገዛዝ ታሪክ "በአኖሌ" ሐውልት ፈርጆ፣ ሰንደቅ ዓላማችንን አራክሶ፣ ታሪካዊ ቅርሶቻችንን "ድንጋይ!" ብሎ ያላገጠው የኢሕአዴግ አገዛዝ፣ ህወሓት የቀረጸለትን "ሕገ ጥፋት" ተገን አድርጎ ነውና ሁለቱን በማሽሞንሞን ሳይሆን በአጥፊዎች የታሪክ መዝገብ ላይ አሥፍሮ ለመሠረታዊና ሥርነቀል ለውጥ ሀገሪቷ ስትዘጋጅ ያኔ በኢትዮጵያዊነት ዋርካ ሁሉም አንድ ሕዝብ! ይሆናል፤ ያኔ ትኩረታችን ወደ እድገትና ብልጽግና ይሆናል።</u>***

*ህወሓት/ኢሕአዴግ እና ሕገ መንግሥቱ ለ28 ዓመት የተከሉት የዘረኝነት አገዛዝ ቀስ በቀስ ወደ ኢትዮጵያዊነት እንቀይረዋለን የተባለው ወይም የተሸፈብን ጉዞ ዛሬ በሁሉም የሀገሪቷ ክፍል በአንድ አሸባሪና አክራሪ ቡድን ብቻ ሳይሆን በመንግሥትም ድጋፍ ሰጪነት ሕፃናት፣ አዛውንት እናት አባትን፣ ወጣቶችን፣ ታዳጊ ሕፃናትን፣ እየፈጀ፣ እያሰቃየ፣ እያፈናቀለ አለበት ደረጃ አድርሶናል። የዚህ እልቂት ተሸካሚዎች ደግሞ በተለያየ የመንግሥት መዋቅሮች ተሰግስገው ሥልጣናቸውን ተገን አድርገው ሲዘርፉ፣ ነዋሪን ለላስቲክ ቤትና ለጎዳና ተዳዳሪነት ሲዳርጉ፣ ታዳጊ ሕፃናትን ሳይቀር ወጣት እህቶቻችንን ሲደፍሩ፣ ወጣቶችን ለአደንዛዥ ዕጽ ተገዢ በማድረግ ሲከብሩ፣ ስሙን ስንጠራው*

እንኳ በአፋችን ምራቅ የሚሞላውን እጅግ ባህላችንንና ሃይማኖታችንን የሚያራክሰውን "ግብረ ሰዶማውያን" እንዲስፋፉ በር የከፈቱትን ሌላም ሌላ ወንጀል ሲፈጽሙ የነበሩ በግልና በቡድን አጥቂ ግለሰቦችን ይዞ "ለውጥ" ያመጣው ቢኖር ሀገሪቷን ወደ አስደንጋጭና አሳዛኝ ዕልቂት፣ የኢኮኖሚ ድቀት ማሸጋገር ነው።

ይህንን የኢሕአዴግ 28 ዓመት አገዛዝ ውጤት በተደጋጋሚ ስንገልጽ ምንጊዜም ይህ አገዛዝ ከዘረኝነት አባዜ፣ ቋንቋንና ዘርን ተገን ከአደረገ አከላለል ሊላቀቅ እንደማይችል ስንጠቁም ነው። እውን ኦነግ ነው አሁን የሚካሄደውን የዘር ዕልቂት ለማስቆም መድረክ የሚሰጠው? እውን እንደ ጀዋር ያለ አሸባሪን አቅፎ ነው የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት የሚገነባው?፡ እውን ኢሕአዴግ ውስጥ ከላይ እስከታች የተሰገሰጉትን "የቀን ጅቦች" አቅፎ ነው ዘረኝነት አፈር የሚለብሰው? ችግሩን ለመፍታት የጨነቃቸው ዶር ዐቢይ "ትምህርት ቤት እዘጋለሁ"፣ ዘረኛ ፖለቲካ ድርጅቶችን ሰብስቤ በውይይት እፈታለሁ፣ የእርስ በርስ ግጭት ነው፣ መፈናቀል፣ መገደል፣ መቃጠል ትላንትም ዛሬም ሆነ ነገ ይቀጥላል፣" ድምጻቸው ነው እውነት ኢትዮጵያን ወደ ዴሞክራሲያዊ ጎዳና የሚያሸጋግረው? እራሷ ለኩሳ "ጭስ ጭስ ይሸተኛል፤ ቤት ሊቃጠል ነው መሰል" ያለችው ዓይነት ጨዋታ ወይም "እራሱ ተንኩሶ፤ እራሱ አለቀሰ" እንዳለችው ተዋናይ፣ ጅራፍን በጥይት እንቀይረውና "ጥይት እራሱ ገድሎ እራሱ ይጮኻል" ዓይነት የኢሕአዴግ ጨዋታ ሊያበቃ ይገባል። በለውጥ አራማጅ ስም የተሸሞነሞነው ኢሕአዴግ እየተጓዘበት ያለው አቅጣጫ ሕዝብ እያስፈጀ፣ ቤተ ክርስቲያን እያቃጠለ፣ ቅርስ እያጠፋ ነውና ጊዜና ዕውቀታችንን ለሀገር አድን ዘመቻ እናውለው እንላለን።

## *<u>የኢሕአዴግ ውህደት</u>*

የሰሞኑ የኢሕአዴግ የውህደት ጉዞ በሂደት ሀገሪቷን ወደ ዴሞክራሲያዊ ጎዳና ያመጣል ብለን ተስፋ ላደረግን አንታለል እንላለን። 27 ዓመት በመለስ ዜናዊ እና በኃይለማርያም ደሳለኝ የተዋሸነው ይበቃል። የሁለት ዓመቱ የዶር ዐቢይ አሕመድ ኢትዮጵያዊነትና የለውጥ ሂደት ያመጣልን ቢኖር በወቅቱ እስቲ ቅድሚያ ወያኔና ኢሕአዴግ ከጫንቃችን ላይ ይውረዱና አናደምጠዋለን በሚል ያላነሳነው በመቶ ሺህዎች ሕይወት የተረከብነውን ባድሜ ለኢሳያስ አፈውርቂ የዕርቅ ገጸ በረከት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መስጠት ነበር። በዚህ የተጀመረው የለውጥ ሂደት ኢትዮጵያዊነትን እየሰበከ ኢትዮጵያን ሊያሳጥን እንዳይሆን የሰጋንበት ሁኔታ ላይ አድርሶናል። በየትኛው የኢትዮጵያ ግዛት በሌላ ዘር ወይም በክርስትና እምነት ተከታዩ የተቃጠለ መስጊድ መኖሩን ባናውቅም "መስኪድና ቤተ ክርስቲያን አሁንም ወደፊትም ይቃጠላልና አትደነቁ" ያሉን ጠቅላይ ሚንስትር እውን እንዘንላቸው ወይስ እንዘንባቸው? "ኢትዮጵያ ለተለያዩ ጥፋት ስትዳረግ አዲስ አይደለምና አታጋግሉ" ሲሉን "በሀገራችን የተከሰቱት ሌሎቹ ቀደምት ጥፋቶች እኮ! በጊዜው ያሉት ነገስታትም ሆኑ መንግሥት ከሕዝብ ጋር ሁነው ለመከላከል ጥረት አድርገዋል፤ የዛሬው ግን እርሶ የሚመሩት መንግሥት ለጥቃቱ አድራጊዎች ከለላ እየሰጠ፣ እሱን አልሰማሁም እያለ፣ የፌደራልና የአካባቢ ፖሊስ ጥቃቱን "ዐይኔን ግምባር ያርገው" ብለው ችላ ሲሉ መንግሥት እራሱ የድርጊቱ ተባባሪ አይደለምን?" ቢባል ምላሽ ምን ይሆን?

አዎ! በኢትዮጵያ የሀገር፣ የሕዝብና ሰንደቅ ዓላማ ፍቅር ሳይኖረው የገዛ አገዛዝ ቢኖር ኢሕአዴግ ነው። <u>የወያኔ/ኢሕአዴግ የመጨረሻው ደረጃ ሀገር የማፍረስ፣ ሕዝብ የማረድ፣ ሰንደቅ ዓላማን መቀየር፣ አብያተ ክርስቲያናትን ማውደም፣ ዳግም እንዳይነሱ የታሪክ ቅርሶችን ማፍረስ፣ መዝረፍ እንደሆነ ገና ከጅምሩ ዓይናችሁን ጨፍኑ፣ ጆራችሁን ዝጉ፣ አፋችሁን ለጉሙ ካልተባለ በቀር እያየን፣ እየሰማንና እየተናገርን ነበር፤ ነውም</u>።

"መልከ ጥፉን በስም ይደግፉ" ካልሆነ በቀር የኢሕአዴግ "ብልጽግና ፓርቲ" መጣ አልመጣ መሠረታዊ የሀገሪቷን ችግሮች ለመፍታት ሳይሆን አገዛዙን በሌላ መልክ ለማጠናከር የሚደረግ ሂደት እንደሚሆን ደርሶ ከማየታችን በፊት መናገር እንችላለን። ተመክሮ ብዙ አስተምሮናልና ዶር ዐቢይ ለኢሕአዴግ መዋሃድ ምነው እንዲህ ተጣደፉ? ሀገሪቷ አኬልዳማ መሆኗ የየዕለት ዜና እየሆነ ምነዋ ውይይት አበዙ? እጅግ በቀላሉ በቁጥጥር ሥር ሊውል የሚችለውን አሸባሪነት ተግባር ምነዋ "የነበረ፣ ያለና የሚኖር" አስባላቸው? ይህ መልዕክታቸው ቄሮዎችን፣ ተገንጣዮችን፣ የዘር ዕልቂት ፈጻሚ አሸባሪዎችን ማበረታታ አይሆንምን?

በእኛ ትንታኔ የኢሕአዴግ ውህደት ህወሓት ከትግራይ ተቀላቀለ አልተቀላቀለ ለጊዜው ትግራይ በወያኔ ቁጥጥር ሥር እንዳለችው ይቀጥላል። ወያኔ/ህወሓት እንደ ኤርትራው መንግሥት ሆነው ሊኖሩ እንደማይችሉ እራሳቸውም ስለሚያውቁት የጀመሩትን የጥፋት በትራቸውን በቀሪው የሀገሪቷ ግዛት ይገፉበታል። በተለይ አማራው ላይ ያነጣጠረ ፍጅታቸው ይቀጥላል። የውህደቱ ውጤት አጋር ድርጅቶችን በመዋጥ ድሮም ስም ብቻ የሆነውን አማራ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (አዴፓ) በመጠቅለል፣ ኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኦዴፓ)ን ማዕከል ያደረገ ፓርቲ ከመመሥረት አይዘልም። ጠ/ሚሩ ለዚህ ሂደት ደግሞ በተለያዩ ቁልፍ የመንግሥት አውታሮች የኦሮሞ ተወላጅ አነጋውያን ባለሥልጣናትን አስቀድመው ሰግስገዋልና አዲሱን "የብልጽግና ፓርቲ" ውስጥ እራሳቸውን ወሳኝ የፓርቲ መሪ በማድረግ በኢትዮጵያዊነት ስም ኦሮሞን ማዕከል ያደረገ የፓርቲ ጉዞ እንደሚሆን አስቀድመን እናስገነዝባለን። ዕድሜ ከሰጣቸው በቀጣይነት በሌሎች ክልሎች ከአሁኑ እራሳቸውን ወደ ፓርቲነት በመቀየር እየተዘጋጁ ነውና (ለአብነት የሶማሌ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ? እና የመሳሰሉት) ኦነግ እና ሌሎች አናሳ የዘር ድርጅቶች ወደ ፓርቲ በመለወጥ ወይም በአዲሱ የኢሕአዴግ ፓርቲ እንዲጠቃለሉ በማድረግ ኦዴፓና ኦነግ የሚመሩት "ኢትዮጵያዊነትን" ካባ የተከናነበ አደገኛና አምባገነን የኦሮሞ ፓርቲ ከመመሥረት እንደማይዘል ነገ የምናየው ይሆናል።

ታሪክ ራሱን ይደግማል የሚባለው ኢትዮጵያችን ጋ ሲሆን ደግሞ ይደጋግማል፣ ይሰልሳልም። በ1970ዎቹ ወታደራዊው መንግሥት አገዛዝ ጊዜ አንድ የኢትዮጵያ ማርክሳዊ ሌኒናዊ ድርጅቶች ሕብረት (ኢማሌድሕ) የሚባል የድርጅቶች ስብስብ ነበር። ይህ ስብስብ በኮሎኔል መንግሥቱና ድርጅታቸው አብዮታዊ ሰደድ ያኮረፉትን አጣጥመው፣ ሌሎቹን በውህደት ስም አክስመዋቸው የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ አደራጅ ኮሚሽን (ኢሠፓአኮ) ቀጥሎም የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ (ኢሠፓ) ተመሠረተ ተባለ። የ"ውህደት" ሂደቱም ቢሆን በስብሰባና መግለጫ ጋጋታ የታጀበና ለወራት የዘለቀ የከተማ ወሬና ሃሜት ርዕስ ነበር።

ሌላው ታሪክ ደግሞ በቀድሞው የአሜሪካን ፕሬዚዳንት ጂሚ ካርተር ደላይነት፤ በአሻግሬ ይግለጡ የደርግ ልዑክ መሪነት፤ ከሻቢያና ህወሓት ጋር ንግግር ሲጀመር ማ ማንን? ወክሎ በንግግሩ እንደሚካፈል ግልፅ እንዲሆን የደርግ ተወካዮች ይጠይቃሉ። የሌሎቹ ማለት የሻቢያም፣ የደርግ ግልፅ ሲሆን የትግራይ ውክልና ብቻ ማለቱ ቅርቃር ውስጥ እንድሚከተው የተረዳው የክፋትና ተንኮል ደቀመዝሙሩ መለስ ዜናዊ ጊዜ ይሰጠን ብሎ ውይይቱን አቋረጦ ወደ ትግራይ ተመለሰ፡ ፡በቀጣይነትም የአማራ፣ ኦሮሞ፣ ደቡብ የሚባሉ ልጥፍ ድርጅቶችን በህወሓት የበላይነት አሰባስቦ በመለስ ዜናዊ ፈላጭ ቆራጭ አመራር መዳፍ ውስጥ የወደቀ ኢሕአዴግ የተባለ አያ ድቡልቡሌ ግንባር ጠፍጥፎ ሠራ። በኢትዮጵያችን ታሪክ ጥቁር ነጥብ ከጣለው የለንደን ውይይትም ወያኔ በምዕራባውያን "መልካም ፈቃድ" ሥልጣን ላይ ሲወጣም እስካሁንም ይህንን የኢሕአዴግ ጭንብል ይጠቀምበታል።

አሁን ደሞ ኢሕአዴግ በውስጥ ችግሩና በዘረኝነት ፖሊሲው ሲንገዳገድ ዕድሜውን በውህደት ስም ለማራዘም ጠ/ሚር ዐቢይ ኦነግን ማዕከል ያደረገ "ብልጽግና ፓርቲ" በመመስረትና "በበሳል"

*አመራራቸው "ኢትዮጵያ" እያሉን በተዘዋዋሪ መንገድ የአንድ ዘር የበላይነት ሊያነግሱ የተወጠነ ሤራ መሆኑን ልንጠቁም እንወዳለን። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ በውህደት ስም የኦሮሞ ፖለቲከኞች የበላይነት የተንሠራፋበት "ብልጽግና ፓርቲ" ይፋ አድርገውልናል።*

*አራተኛው የታሪክ ድግምግሞሽ ኢዜማንና ሌሎች ተፎካካሪ ድርጅቶችን አጠቃለው ኦሮሞ መር አውራ ፓርቲ ይፈጠር ይሆን? የዚህ ተንኮል ሂደት በቀጣይነት የዘር ድርጅት አያስፈልግም በሚል በተለይ በአማራው በኩል እራስን ለመከላከል የተደራጁ የዘር ድርጅቶችን በማፍረስና በመዋጥ ኢትዮጵያዊነት ቡልኮ የለበሰ የኦነግ፣ ኦዴፓና ጠቅለል ስናደርገው የኦሮሞ መር ፓርቲ ሀገሪቷን በመቆጣጠር አፍኖ መግዛት ሌላው ዘዴ ነው። ባንዳ፣ አሽቃባጭና ከሀዲ በየጊዜው ያልተለያት ሀገራችን፣ ፖለቲካ ኑሯቸው ሊያደርጉ በቋመጡ አድርባዮችና ተገለባባጭ ፖለቲከኞች ለዚህ አዲስ የውህደት ፓርቲ አመቺ የማዕዘን ድንጋይ ናቸውና ትርፍራፊ እየሰጡ "አይዞህ! ቡቺ" ማለት ብቻ በቂው ነው።*

*ይህ ሂደት ሀገራችንን በዚህ ዘዴ ሊቆጣጠር ለፈለገው የኦነግ ኃይል ሊያስከትል የሚችለውን ጥፋት እየቃኘን፣ "አጥፊ ላጥፊ አብረህ አዝግም" እንዲሉ፤ በመሰባሰብ ትግራይን የተቆጣጠረው ህወሓትና የዚህ ፕላን አቀናባሪ የሻቢያው ኢሳያስ አፈወርቂ ጥምር ስብስብ ኢትዮጵያን በመቆጣጠርና ከአረቡ ዓለም በሚያገኙት ድጋፍ ለምሥራቅ አፍሪካም ሆነ ለሌላው ዓለም አደገኛ የሆነ "የማፍያ" ቡድን እንዳያቆጠቁጥ ልንጠነቀቅ ይገባናል።*

*ከላይ የጠቀስናቸው ሦስቱም የመንግሥት አካሎች (ደርግ፣የመለስ ኢሕአዴግ እና የዶር ዐቢይ "ለውጥ" አራማጁ) ከሀገሪቷ መሠረታዊ ችግር ይልቅ የሚያሳስባቸው እንደ እስስት እየተቀያየሩ እንዴት አድርገው የመንግሥታቸውን ዕድሜ እንደሚያራዝሙ ነው። ነፍሱን ይማረውና "አልማዝን አይቼ አልማዝን ባያት . . ." እንዳለው ጥላሁን ገሠሠ ኢሕአዴግ በሉት፣ ብልጽግና "ከዝንጀሮ ቆንጆ ምን ይመራርጧል" ነው።*

***<u>መሠረታዊ የሀገሪቷ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ ችግሮች ያለውን አገዛዝ  በተለያየ የፓርቲ ስምና ውህደት በማገለባበጥ አይፈታም። የሕዝብ ፍላጎት ዘርና ቋንቋን ተገን ያደረገው አከላለል አብቅቶ፣ አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ሰንደቅ ዓላማችን ተውለብልቦ፣ ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት ከተራራው ጫፍ ሁኖ፣ ለትውልድ ሚተላለፍ ኢትዮጵያዊነትን መሠረት ያደረገ ሕገ መንግሥት ተግባራዊ ሁኖ ሁሉም ጎሳ/ነገድ በአንድነት፣ በፍቅር የሚተጋላትና ትኩረቷን ወደ ልማትና ዕድገት ያደረገች ኢትዮጵያ ማየት ነው።</u>***

*ይህ የመረረ ጩኸታችንና ጽሁፋችን እንኳን በሀገራችን በየትኛውም ዓለም ከምንም በላይ የሰው ልጅ እልቂት ያመናልና ነው። የሰው ልጅ እልቂት ድሮም ያለ ነው፣ ዛሬም፣ ወደፊትም ይኖራል ብለን መፈላሰፍ የሚቃጣን አይደለንምና ነው። የሰው ልጅ አፈር እየለበሰ  ሀገራችንን እንወዳለንና ሉዓላዊነቷን የጠበቀች የጀግኖች ሀገር እንጂ የአሸባሪዎችና የአምባገነኖች መፈልፈያ እንዳትሆን ያሰጋናልና ነው። በመላ ሀገሪቷ እየታየ ያለው የወገኖቻችን ዕልቂት ህሊናን ቆጥቁጦ፣ እንቅልፍ ነስቶ አጣዳፊ መፍትሄ መሻት ሲገባ ሥልጣንን "ዘላለማዊ" ለማድረግ ቀዳሚው ፓርቲ ምሥረታ ሲሆን ያስተዛዝባል፣ ያሳዝናል።*

***ምን ማድረግ አለብን?***

*የዘር ጭፍጨፋው በተለይ አማራው ላይ ያነጣጠረው ተጀምሯል። ቤተ ክርስቲያናትን ማቃጠሉ፣ ምህመናንን ማሳደዱ፣ ገዳማትን መውረሩ ተጀምሯል ይቀጥላል። የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት መለያ ሕፃናት እና ወጣት ሴቶችን አስገድዶ የመድፈር ዘግናኝ ድርጊት ትላንትም ነበር ዛሬም አሸባሪው ቡድን ተረክቦታል። መንግሥት አለሁ በሚልባት ሀገር ከትላንቱ 18 ባንኮች ዘረፋ በቀጣይነት ፋብሪካዎችን ማቃጠል፣ ሆቴሎችንና የንግድ ቤቶችን ዘረፋው ተጧጡፏል። ከአንዱ ክልል ወደ ሌላው የሚደረግ እንቅስቃሴ በስጋትና በፍርሃት የታጀበ ከሆነ ሰንበትበት ብሏል። የጥቃት ቦታ የሆኑት ዩንቨርስቲዎች ተማሪዎቻቸው አስጠጉን! እያሉ በየቤተ ክርስቲያኑ እየተከማቹ ነው፣ ሌላም ሌላ። ለዚህ ሁሉ መፍትሄው እንደ መንግሥት ውይይት አለያም **"የነበረ ያለና የሚኖር"** ነው ብሎ አለመደነቅ መሆኑ እየተነገረን ነው።*

*በመሆኑም የሕዝባችን አቅሙ፣ የወጣቱ ጉልበቱ፣ የሴቶች እህቶቻችን ጥንካሬ፣ የአዛውንቶች ጀግንነታቸው፣ የሃይማኖት አባቶች እግዚዮታና እንደየእምነቱ ጸሎቱ ለሀገራችን አንድነት ለሕዝባችን ደህንነት ምላሽ የሚሰጠው ማንቀሳቀሻ ቁልፉ በመሰባሰብና አንድነታችንን በማጠናከር ነው። ይህ አንድነት ተግባራዊ ከሆነ ዘረኝነትና ዘረኞች ኢምንት ናቸውና በነው ይጠፋሉ።*

*እውን ወያኔ/ህወሓት ቤተመንግሥቱ መቀሌ ይሆናል ብሎ የገመተ ነበርን? "ኢትዮጵያዬ" ድምጽ የሚወጣው መሪ ከወያኔ/ኢሕአዴግ ብቅ ይላል ብለንስ ነበርን? መለስ ዜናዊ እግዚአብሔር ይማርህ ሳይባል አፈር ይደፍረዋል ያልንስ ስንቶቻችን ነን? ከሱ ሞት በሳምንታት ውስጥ በቁማቸው የተፈነገሉት ጳጳስ አቡነ ጳውሎስ እውን ይህችን ዓለም በዚ ቅስፈት ይሰናበታሉ ያለስ እስቲ እኔ ነኝ ይበል? እናማ አምባገነኖች፣ ዘረኞች፣ አሸባሪዎች አወዳደቃቸው ከንቱ የከንቱ ከንቱ መሆኑን ብንረዳም በምን መልኩ፣ ከየት አቅጣጫ፣ መቼ የሚለውን ምላሽ የሚሰጠው ፈጣሪ ኢትዮጵያን እንደሚያድናት አንጠራጠርም።*

*በሀገራችንና ሕዝባችን ላይ ያንዣበበው ቁጣና እልቂት ለወንጀለኞች፣ ለሀገር ከሀዲዎች፣ ለቀስተ ደመና "ረጋጮች"፣ ለአራጆችና በኢትዮጵያ ስም ለሚነግዱ አስመሳዮች ነውና "ለአጥያን የዘነበ ለጻድቃን መትረፉ"ን ብንረዳም እምነት፣ ጽናትና ተስፋን ተገን አድርገን በመነሳት ኢትዮጵያንና ሕዝባችንን ለማዳን ከእኛው ሌላ ማንም አይመጣልንምና ጊዜ አንስጠው፤ "እስቲ እንያቸው" እያልን አንለቅ።*

*ከቅርቡ ታሪካችን ቢያንስ እንማር። በዘመነ ቅንጅት ቁራጥ አቋም ከመውሰድ ይልቅ የመለስ ዜናዊን መሠሪነት እያወቅን "እስቲ እንያቸው" ስንል ያበቃለትን የዘረኝነት አገዛዝ 15 ዓመት አዘልነው። የምንሰጠው ድጋፍና ማበረታታት በጭፍን ተጎንብሶ እግር ለመሳም ሳይሆን ከሀገርና ሕዝብ ጥቅም አንፃር ቢሆን ይመረጣል። አንዴ ድጋፍ ሰጥተናልና "ከአፈርኩ አይመልሰኝ" ጉዞ አዋጭ አይደለም። ልደቱን "ማንዴላ" አድርገን ያመለጠን ጊዜ ይታወሰን። ስዬ አብርሃና ገብሩ አሥራትን "መሪዎቻችን" ብለን መድረክ መድረክ ጭፈራችን የት እንዳደረሰን አንዘንጋ። ዛሬም ወደፊትም ጩኸታችን ለሀገራችን፣ ለሰንደቅ ዓላማችን ለሕዝባችን ከሆነ እምዬ ኢትዮጵያ አሸናፊ እንደምትሆን ጥርጣሬ አይግባን።*

*ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!*
*ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይባርክ!!!*
"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"
ኅዳር 12 ቀን 2012 ዓ.ም. (December 22, 2019)

<u>ማሳሰቢያ ፤</u>

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» «***ኢትዮጵያችን***» ልሳን በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጩት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- «አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ» መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org , www.ethiopiachen.com
ምሥለ ገጽ ፡ 1H1H Ethiopiachin